<u>ሠንጠረዥ ሁለት</u>

**ክፍል አንድ**

<u>ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች</u>

የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

1. አውሮፕላን በዓለምዐቀፍ ትራፊክ እንቅስቃሴ ውስጥ ባለበት ጊዜ ተሳፋሪ መንገደኞች እና የአውሮፕላኑ ሠራተኞች በጉዞ ወቅት የሚጠቀሙባቸው በነፃ የሚሰጡ ዕቃዎች፣

2. የዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱለር ሚሲዮኖች ወይም ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ የዲፕሎማቱ እና የቆንስላው ቤተሰቦች ወደአገር የሚያስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዟቸው በዲፕሎማቶች መብትና ጥቅም ደንብ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

3. የውጭ አገር መንግሥታት፣ ዓለምዐቀፍ ድርጅቶች ወይም የዕርዳታ ድርጅቶች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ባደረጉት ስምምነት ወይም በዲሎማቶች መብትና ጥቅም ደንብ መሠረት ወደአገር የሚያስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዟቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

4. የአካል ጉዳተኞች ወደአገር እንዲያስገቡት የተፈቀደ ለአካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ አንድ የግል ልዩ ተሽከርካሪ፣

5. በአደጋ የተጐዱ ሰዎችን ለመርጃ እንዲውሉ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ወደአገር የሚያስገባቸው ዕቃዎች፣

6. ወደአገር የሚገቡ መንገደኞች ይዘዋቸው የሚመጡ አግባብ ባለው ሕግ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

7. ሚኒስትሩ በሚፈርመው ወይም በሚያፀድቀው ስምምነት የተፈቀዱ በዕርዳታ ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች የሚያገለግሉ ወደአገር የሚገቡ ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

8. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ወይም የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ወደአገር የሚያስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዙዋቸው በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

9. በኢንቬስትመንት ማበረታቻ ደንብ መሠረት ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ኢንቬስተሮች ወደአገር የሚያስገቧቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

10. በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ለ" የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

## ክፍል ሁለት

## ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ አገልግሎቶች

1. የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

   ሀ/ ለዲፕሎማቲክ እና ኮንሱላር ሚሲዮኖች ወይም ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ የደፕሎማቱ እና የቆንስላው ቤተሰቦች የሚሰጡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች፣

   ለ/ የውጭ አገር መንግሥታት፣ ዓለምዐቀፍ ድርጅቶች ወይም የዕርዳታ ድርጅቶች በዓለም ዐቀፍ ስምምነት ወይም በዲሎማቶች መብትና ጥቅም ደንብ በተመለከተው መሠረት የሚያገኙዋቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች፣

2. <u>ትርጓሜ</u>

ለዚህ ሠንጠረዥ አፈፃፀም "ዓለምዐቀፍ ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ መንግሥት እና በውጭ አገር መንግሥት ወይም ዓለምዐቀፍ ድርጅት ወይም የዕርዳታ ድርጅት መካከል ለኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የሰብዓዊ ዕርዳታ ወይም አስተዳደራዊ ድጋፍ ለማድረግ የተደረገ ስምምነት ነው፡፡